# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኤፕሪል 11-20/2023 የነበረው የአየር

## ሁኔታ ግምገማ እና

## ከኤፕሪል 21-30/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2023
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ..... 3
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... 5
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20 /2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ..... 6
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20 /2023 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ..... 7
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ..... 7
እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... 8
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... 8
እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... 9
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... 9
እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ..... 10
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-ሜይ1, 2023 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ. ..... 10
ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-ሜይ1, 2023 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲ.ሴ ..... 10
እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... 11
እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... 11

# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ


ባለፉት አስር ቀናት በኤፕሪል በመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በሀገሪቱ ደቡባዊ አጋማሽ፣ ምሥራቅና ምዕራብ አካባቢዎች ሲዘንብ የነበረው ዝናብ ባለፉት አስር ቀናት ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ መልኩ ከመቀጠሉም ባሻገር ከአስሩ ቀናት አጋማሽ በኃላ ወደ ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ ዝናብ ተስተውሏል። በመሆኑም የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ በዚህም መሠረት በአስሩ ቀናት ውስጥ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እሰከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎች መጠኑ ከ30 ሚ.ሜ የበለጠ ከባድ ዝናብ ነበራቸው። ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በሀረር 30.6፣ በማሻ 36.7፣ በደልፋጊ 42.3፣ በአይራ 32.2፣ በአልጌ 34.0፣ በአቦቦ 40.0፣ በደብረ ታቦር 42.5፣ በሞያሌ 53.0፣ በቡሬ 38.3፣ በጅንካ 72.8፣ በግኒር 42.0፣ በተርጫ 30.2፣ በባቲ 30.8 እንዲሁም በኮምቦልቻ 47.0 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

በሌላ በኩል በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ፀሐያማና ሞቃት የአየር ሁኔታ ከመዘውተሩም በተጨማሪ አንፃራዊ የሙቀት መጨመር ያሳየ ሲሆን፤ በተለይም በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ዳርቻዎች በሚገኙ ቆላማ አካባቢዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ35 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ከ35 ዲ.ሴ በላይ የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል በጎዴ 39.4፣39.6፣ በቻግኒ 36.0፣ በመተሃራ 36.4፣36.6፣ በአቦቦ 35.4፣ በዳልፋጊ 37.0፣ በገዋኔ 37.4፣ 37.8፣ 38.4 በአይሻ 37.5፣ 38.2፣ በጋምቤላ 37.2፣ በሰመራ 38.2፣ በዕፅቃ 38.0፣ 38.4፣ በሚሌ 38.5፣ 39.0፣ በአዋሽ አረባ 39.0፣ በቀብሪደሃር 39.0፣ በፓዌ 39.6 ዲ.ሴ ሲሆን፤ በተጨማሪም በጥቂት አከባቢዎች ላይ ደግሞ ከ40 ዲ.ሴ በላይ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በአልያ 40.4፣ በጋምቤላ 40.6፣ በአቦቦ 41.2፣ በፉኚዶ 41.5፣ በመተማ 41.0፣41.6፣43.0፣ በጎዴ 44.6፣ በዱብቲ 41.2፣ 41.5 ዲ.ሴ የደረሰ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን እንደተመዘገበ ከየጣቢያዎቹ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከአማራ ከምዕራብ ጎንደር በስተቀር ሁሉም ዞኖች፤ ጋምቤላ፤ ከአፋር ዞን 3 እና 5፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፤ በአዲስ አበባ፤ በሶማሌ፤ በድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ5-135 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ በዋግህምራ፣ የመካከለኛውና የደቡብ ጎንደር፣ የደቡብና ምስራቅ ጎጃም፣ በደቡብና ሰሜን ወሎ፤ ጋምቤላ፤ ከአፋር ዞን 3 እና 5፤ አብዛኛው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የደቡብ ኦሞ ዞን፤ ከኦሮሚያ የቄሌምና የምዕራብ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ የባሌና ምስራቅ ባሌ፣ የአርሲና የምስራቅ ሀረርጌ ዞኖች፤ ከሶማሌ የዳዋ፣ የሊበን፣ የአፍዲር፣ የኤረርና የነጎ ዞኖች፤ በአዲስ አበባ፤ በድሬዳዋና ሀረሪ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ መጠን የተመዘገበ ሲሆን፤ በተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመደበው ያነሰ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20 /2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነዉ የኤፕሪል ሁለተኛው አስር ቀናት ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከባለፈዉ አስር ቀናት በተለየ የእርጥበት ሁኔታው የመጨመር አዝማሚያ ታይቶበታል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲኖራቸው ያስቻለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ወቅት ሰብሎችም ሆነ በአካባቢዎቹ ለሚበቅሉ ቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት በጎ ጎን ነበረው። በተጨማሪም ወደ ምዕራብና ደቡብ ምዕራብ በመስፋፈት ላይ የነበረው እርጥበት የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለሚዘሩ አካባቢዎች አዎንታዊ አስተዋፅዖ የነበረዉ ሲሆን፤ በተጨማሪም በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ መጠኑ ከ30 ሚ.ሜ የበለጠ ከባድ ዝናብ የተመዘገበባቸው ሲሆን፤ ከዚሁም ጋር ተያይዞ የተገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በተለይም ውኃ አጠር ለሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውኃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ላይ በተወሰነ መልኩ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በሀገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ላይ ማለትም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ከ35 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን፤ ይህም የነበረው ፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ በአካባቢው ከነበረው የእርጥበት እጥረት ጋር ተዳምሮ በወቅቱ አጠቃላይ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ እንዲሁም በአርብቶ አደሩ አካባቢ የእንሰሳት መኖና ውኃ አቅርቦት ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረዉ (ካርታ 4 )።


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኤፕሪል ሁለተኛው አስር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ስንመለከት አብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ኦሞ ጊቤ ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና መካከለኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በጥቂት መካከለኛው እና ታችኛው አዋሽ፣ መካከለኛ ምስራቅ አባይ፣ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ የተለያየ መጠን ያለው እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፤ የተገኘው እርጥበት በአስር ቀናት ከነበራቸው የትነት መጠን አንጻር ሲገመገም ከመጠነኛ እስከ እርጥበታማ ነበራቸው። የተቀሩት የታችኛው ዋቤ ሸበሌና ገናሌዳዋ፣ ኦጋዴን፣ የላይኛው አባይ፣ አብዛኛው ተከዜ እና አፋርደናከል ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ እንደነበር ተስተውሏል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እስከ አፕሪል የመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ጋር ተያይዞ ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተለይም የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን የሚገባው እርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በደቡብ አጋማሽ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት ይኖራል፡፡ እንዲሁም በመጠን ረገድም በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖርና አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ቡኖ በደሌ የሸዋ ዞኖች፣ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ፣ ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ የአርሲ ዞኖች፣ የባሌና ጉጂ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፤ ሁሉም የሶማሌ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማና ክልል ዞኖች ፤ከጋምቤላ ክልል የመዥንገር እና የአኝዋክ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ደቡብ ጎንደር ዞኖች ፤ከትግራይ ክልል የመካከለኛው፣ የምሥራቅና የደቡብ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአህዛዊ ትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-ሜይ1, 2023 የሚኖረዉ የዝናብ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-ሜይ1, 2023 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኤፕሪል የሶስተኛው አሥር ቀናት የደቡብ አጋማሽና የደቡብ ምዕራብ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች የሚጠቁሙ ሲሆን አልፎ አልፎም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ የበልግ ሰብል አብቃይ እና የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ለሆኑ አካባቢዎች አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን ከዚህም ጋር ተያየዞ ቀደም ብለው ለተዘሩ ለበልግ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም እንደ በቆሎና ማሽላ የመሳሰሉ የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚኖር የሚጠበቅ በመሆኑ አርሶ አደሮች ተገቢ የሆኑ ግብዓቶችን በማካተት የእርሻ ሥራውን በተሟላ መልኩ ማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡ በአንጻሩም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለከብቶች መኖና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማበልጸግና ለወቅቱ የግብርና  ስራ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንም  በተወሰኑ ውሀ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሣዎች ላይ የውሃ መተኛትና የአፈር መታጠብን ሊያስከትል ስለሚችል ለዚሁ ችግር ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል። በሌላ በኩል እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ የእርጥበት ማሰባሰቢያና ማቆያ ዘዴዎችን ተግባራዊ በማደረግ በመስራት በመካከል ለሚገጥሙ ደረቅ ሰሞናት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የማድርግ ስራዎች ተጠናከረው እንዲከናወኑ ይመከራል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኤፕሪል የሶስተኛው አሥር ቀናት በተለይም የደቡብ አጋማሽና የደቡብ ምዕራብ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እንደሚጠናከሩና በአብዛኛው ተፋሰሶች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት

እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች የሚጠቁሙ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በአንዳንድ ተፋሰሶች ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ሊያገኙ እንደሚችል ይጠበቃል። በተለይም በአብዛኛው አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ የላይኛውና መካከለኛው አባይ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በታችኛው ተከዜና በታችኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ የሚኖራቸው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የገፀ-ምድር እና የከርሰ-ምድር የውሃ ኃብትን ከማዳበር አንጻር በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ሊከሰት ከሚችለው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለይም በተዳፋት አካባቢ በሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በህይወትም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት ለማደረስ የሚችል አቅም ሊኖረው ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን የቅድመ ጥንቃቄ ዝግጅት እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራሉ።